# የከበደ ጉዞ

ከሀማ ቱማ

ሕይወት ጉዞ ነው:: ረጅም ጠመዝማዛ ፣ ባለውጣ ውረድ:: ትግልም ሕይወትን ገላጭ ነውና አድካሚ ጉዞን ያዘለ ነው:: አለመታደል ሆኖ ዛሬ ትግልን ሳይኖሩ ማለትም ጉዞን ሳይጀምሩ ጉዞን የሚተቹ በዝተዋል:: ታገሉ ታከቱ አለና ይላሉ ግን የት ደረሱ ፣ መቸስ አሸነፉ ይላሉ:: የፍልስጤሙ ዝነኛው ገጣሚ ዳርዊሽ በመታገል ሞትንና መርሳትን አቸነፍን፣ በመኖራችን ና ትግል በመቀጠላችን ደግሞ በጠላት ላይ የነገን ድል አበሰርን ነበረ መልሱ:: ትግል ሕል ውና ነው፣ ሰውን ሰው የሚያደርገው:: ፀንተው የታገሉ ቢሰዉም ሕያው ናቸው:: በትግል መ ሞት ሕይወት ዳግም ትንሳዔ ልደት የሚባለው ለዚህ ነው:: ረጅምና ከባድ ጉዞ-- ሕይወትን ገላጭ:: ከባድ ጉዞ በአንድ በኩል --በሌላ ደግሞ አቶ ከበደ ሚካዔልን ለመዘከርና የተጓዙበት ንውጣ ውረድና ብርሀነ ሕሊናቸውንም ለማስታወስም ነው:: እሳቸውም ቢሆኑ በአንድ የታሪ ክ አጋጣሚ መንገድ ስተው እንደነበር ሳንረሳ::

*“ ጋሬጣና አሸሟጣጭ አንድ ነው ባሕሪያቸው*
*የሚያልፈውን ሁሉ በመቦጨቃቸው*
*ጋሬጣስ ቦጭቆም ያስቀራል በጥሶ*
*አሸሟጣጭ ክፉ ነው ይከተላል ነክሶ :: ”*

ለኢትዮጵያና ለሕዝባ ቆርጠው የታገሉትን ነጋ ጠባ በመቦጨቅ ዘመቻ የተካኑ ብዙ ናቸው:: ዛሬም ድርጅቶችን በአሉባልታ እያጠቁና እየሰነጣጠቁ አሉ:: ህልውናቸው ክህደት ነው:: ነ ፍሳቸው የምትንቀሳቀሰውም ሌሎችን በማጥቃትና ሰማዕትን በማንቋሸሽ ነው:: ተቃዋሚ ድ ርጅቶች መሀል ሰላምና ስምረት እንዳይሰፍን ከወያኔ ቅጥረኞች ባልተናነሰ ይራወጣሉ:: ደር ግና ወያኔ ለምሳሌ በኢሕአፓ ላይ የነዙትንና እየነዙ ያሉትን ሁሉ ነፍሰ ዘርተውበት ያናፍሳ ሉ:: በሰበብ አስባቡ ከየደርጅቱ የኮበለሉ ደግሞ የዚህ ዘመቻ ወዶ ገባ ጀሌዎች ሆነዋል:: መ ቦጨቁ ቢያከትም ደግ ነበር:: በዚህ አሳዛኝ ስምሪት ላይ ላሉት ደግሞ አቶ ከበደ ሚካዔል የ ሚከተለውን ብለዋል፣

*“ ትምህርት ካልጨመረ በተፈጥሮ ዕውቀቱ*
*ሕፃን ልጅ ይሆናል ሰው ከነሽበቱ ” ::*

ደግሞ ደ.ጋግሞ ተመክሮን ዘንግቶ ሕፃን መሆኑና ለጠላት ማመቸቱ ማብቃት ያለበት ነው። ማወቅ መማር የሚገባቸው የወያኔ ሰለባ ሆነው በአሉታዊና አፍራሽ ጎዳና ይነጉዳሉ። ይህ ሁኔታ ካልተቀየረ የሕዝብ ትግል ድል የነገ የነገ ምኞት ሆኖ ይቀርብናል።

*"ብዙ ሰዎች አሉ ባሕሪያቸው የከፋ*
*ዐዋቂዎች ተብለው ስማቸው የጠፋ።*
*በዕውቀት ተመስግነው በጣም የተማሩ*
*ጥበብን ዕውቀትን የተመራመሩ ፤*
*ግን፤ በሕይወታቸው ባለም ላይ ሲኖሩ*
*ብዙ መጥፎ ሥራ በሰው እየሰሩ*
*ተሰድበው፤ ተጠልተው ተንቀው የቀሩ"*

ዛሬ የሕዝብ ጎራን መሰረታዊ ድክመት ስንመረምር ዐዋቂዎች ተብለው ብዙ መጥፎ ስራን የሚሰሩ መበርከታቸው መሆኑን መካድ አንችልም። ባህሪያቸው መክፋቱ ብቻ ሳይሆን በጥቅም በመገዛት፤ ቤት አለን ንግድ አለን በሚል አያሌዎች ከሀገር ጠላት ጎራ ተሰልፈዋል። ባንዳ ይበረክታል አርበኛ ግን ይሞታል የሚለው ግንዛቤ ከአፄው ጊዜ ጀምሮ ሀቅ ተብሏልና ከመኖር መበርከት ባዮች ሁሉ ጭፍን አድርባይነትን ሲያቅፉ የሚያፍሩ አልሆኑም። ወያኔን ጊዜ እንስጠው፤ እንታገሰው ያሉ ሁሉ ለአረመኔው አገዛዝ ደ.ጋፊ ሆነውታል። ወደ ትጥቅ ትግል መሰማራት ሐጢያት ነው ያሉት ሁሉ ወደዱም ጠሉም ወያኔን ረድተውታል። ዛሬ ምንም አዎንታዊ የሁኔታ ለውጥ በሌለበት ከወያኔ ጋር ዕርቅና ሰላም የሚሰብኩ፤ መቻቻልን የሚመክሩ ወደዱም ጠሉም ሁሉም በተጨባጭ የወያኔ አጋሮች ናቸው ። ለሚቹ ፀረ ሕዝብ ከልብ ያለቀሱ የሚናቁ ናቸው። አወቅን ተመራመርን በቃን መጠቅን ባይ አንዳንድ ምሁሮች ዕውቀታቸው ዜሮ እየሆነና መጥፎ ስራ እየሰሩ በሕዝብ ተጠልተው፤ ተሰደብውና ተንቀው እየቀሩ ናቸው። የዶክተር ፕሮፌሰር ታፔላ ለጣፊዎች ዝናቡ ሲያባራ ባሩድ ሽታ ሳይደርሳቸው ሰልፋቸው ሕዝባዊ አልሆን እያለም ማስቸገሩ የሚደበቅ አይደለም። ይህም ማብቃት ይኖርበታል ።

*"ዐውቃለሁ ትላለች ዕውቀቷን በታትና*
*ክልፍልፍ እብድ ነች እመት ድንቁርና*
*የጥፋቷ ብዛት ልክ የለውምና "*

አላዋቂ ሳሚ ይላል የሀገራችን ሰው። ከሁሉም የሚከፋው ደግሞ አለማወቅን ራሱን አለማወቅ ነው። ጥራዝ ነጠቆች ታሪክን ከማወቅና ከመማር ፊንታ የድርጅቶችንም ፤ የትግልንም ሆ

ነ--በጣሙን የከፋው ደግሞ--የሀገርንም ታሪክ አጣመው ይፅፋሉ። የኢትዮጵያ ሕልውና መ ቶ ዓመት አይሞላውም፣ አማራው ሕዝብ ጨቋኝ ነው፣ ኢትዮጵያዊ አይደለንም፣ ኢትዮጵያ ቅኝ ገዢ ናት፣ ኢሕአፓ ሀገር አስገነጠለ፣ ሕዝብን ለትግል ተነሳ ብለው አስጨረሱት፣ ወያኔ ሀገር ወዳድ ነው፣ ወዘተ የሚሉ አሉ። ማለት ብቻ ሳይሆን አያሌ መፅሀፍትም በወያኔ እርዳ ታና ድጋፍ ተፅፈው ተሰራጭተዋል። ሕዝብን እርስ በርስ የሚያጣሉና በውሸት ታሪክ ላይ የ ተመሰረቱ መፅሀፍትም በሰፊው ተሸጠዋል። ያበደ ድንቁርና !

*" ደግና ክፉውን እያደባለቀ*
*መንፈሱ ለይቶ ፍርድ ካላወቀ*
*ድካሙ ከሆነ ለጌጡ ለልብሱ*
*ልፋቱ ከሆነ እስኪሞላ ከርሱ*
*ካላቀረበለት ኅሊናው ወቀሳ*
*በምኑ ይበልጣል የሰው ልጅ ከእንስሳ" ።*

ዛሬ በኢትዮጲያ ሕዝብንና ሀገርን የጎዱ ከርስ አደሮች መበርከታቸው ምስጢር አይደለም። ደርግ ደም አደር ተብሎ ነበር--ደም ያክለፈለፈው አረመኔ ቡድን ነበርና። ፕሮፌሰር አሥራ ት ደግሞ ሆዳም.... ብለው ለወያኔ ያጎበደደውን ከሰው ነበር። ለትግል ወይም ለተቃዋሚ ድ ርጅቶች አዋጣ ሲሉት "መናጢ ድሀ ነኝ" እያለ ለወያኔ ባዛርና ገንዘብ አምጡ በሺና በሚሊ ዮን ደረጃ ሲከፍል የሚታየውን ነው። ልፋቱ ለግል ጥቅሙና ለከርሱ ብቻ የሆነውን። ስንቱ ነው ሮጦ ለወያኔ ግድብ ገንዘቡን የለገሰ? ከዚህ ውስጥስ ስንቱ ነው ለተቃዋሚ ድርጅቶች (ይ መቸኛል ላለው መርጦ) ገንዘብ የሰጠ ? ድርጅቶችን ምንም አልሰሩም ብሎ አጥብቆ ተቺ መቼሰ የሚወቅሰውን ድርጅት በሚገባ ረዳ? ፍጠኑ ሙቱሉን የሚባሉትን ድርጅቶቸስ ማን ደጀን ሆናቸው? በግንቦት 20 ድግስ አስረሽ ምቺው የሚለው ራሱን ስደተኛ ባይስ ቁጥሩ ብ ዙ አይደለም? የብዙዎች እንስሳነት ለከርሳቸው በማደራቸውና የሀገራቸውንና የወገናቸውን የሰቆቃ ጩኸት አልሰማ ከማለታቸው የሚታይ ነው። ሰው ኅሊና ከሌለው እንስሳ ነው። ኅሊ ናውን ማጅራት መትቶ ራሱን ለወያኔ የሚሸጠውም እንስሳ መባሉ ትክክል ነው። ቤት ሰርቻ ለሁ፣ ንግድ ፍቃድ ሰጥተውኛል፣ በሕይወትም በሁሉም ስግብግብነት፣ ከርስን ከሀገርና ከወገ ን ማስቀደም፣ በሆድና በፍርሐት መሸነፍ--ይህ ሁሉ ያሰድባል፣ ያስወቅሳል። ሀገርንም በጣም ይጎዳል። ለሆዳም ሀገሩ ሆዱ ነው የተባለው ሀቅ ነው።

*"አንዳንድ ሰው አለ መንፈሱ ደካማ*
*ደጋግመው ሲነግሩት ምንም የማይሰማ*
*ዘርዝሬው ሲያስሬዱት አዳምጦ ጨርሶ*

*ጥያቄ ያመጣል እስር ተመልሶ*
*የዕውቀቱ መደንዘዝ ያሰኘዋል ከቶ*
*ውስጡን የሚሰራጭ በደም ስሩ ሞልቶ*
*ቀዝቃዛ ውሃ ነው ደም መሆኑ ቀርቶ "::*

ስለወያኔ ማንነትና ምንነት ከ20 ዓመት ያላነሰ ያውም በደም የተገበየ ተመክሮ አለን:: ወያኔ ስልጣን ከመድረሱ በፊትም ስለ ፀረ ኢትዮጵያነቱ በቂ ቅስቀሳ ተደርጎ ማስጠንቀቂያም ተሰ ጥቶ ነበር:: ሰሚው ብዙ አልነበረም:: መርዘኛውን እባብ በኪስ የከተቱና መለስን ከነጭፍሮ ቹ ልጆቻችን ናቸው ያሉም ነበሩ:: ተማሪዎች ተቃውመው ሲገደሉ፣ ወያኔና አጋሮቹ በኢሕ አፓዎች ላይ ተረማምደው ለስልጣን ሲበቁ እባብን በእንጭጩ በማለት ፈንታ ለልጆቹ ጊዜ እንስጣቸው ብለው የተሟገቱም ብዙዎች ነበሩ:: ከመቅፅበትም የየብሄረሰብ ቡድን አቋቁመ ው ከወያኔ ጎን ተሰልፈዋልም:: ይህ ሁሉ ያኔ ነው:: ዛሬስ? የተለየ ሁኔታ አለ ወይ? አንድ እ ርምጃ ወደፊት ሁለት ወደኋላ ነውን? ነው አይደለም ብሎ ንጥር ባለ ሁኔታ መደምደም ከባ ድ ነው:: የታሪክ ጎማ በአስፋልት ሁሌም አይጓዝምና-- ውጣ ውረዱ፣ ኮረኮንቹ ብዙ ነው:: ወያኔ ፀረ ሕዝብና ፀረ ኢትዮጵያ መሆኑ መነገር ብቻ ሳይሆን በገቢርም በንፁሐን ደም ታጅ ቦ የተረጋጋጠ ነው:: ይህን ሀቅ መቀበል አቅቷቸው አንጎላቸው ደንዝዞ ዛሬ ነገ ከወያኔ ዕርቅ፣ ከወያኔ ሰላምን፣ ከወያኔ ለውጥን የሚጠብቁ እውነትም ደማቸው ቀዝቃዛ ውሀ ነው:: ሞኝን ሳይወለድ ማስወረድ ወደሚል ፅንፍ ባንሄድም በቁማቸው ሞተዋል ማለትም ይቻላል::

*" አይገኝም ከቶ ቢፈልጉ ዞሮ*
*መስማት ከማይፈልግ የባሰ ደንቆሮ " ::*

ከተመክሮ የማይማር ሲነግሩት የማይሰማ ለሀገር የማይበጅ ዜጋ ነው::

*" እንዳይነጋ እንዳይመሽ ብልጎት ተገኝቶ*
*ጊዜውን መከልከል እንዳይቻል ከቶ*
*እንዲሁም ባለም ላይ አለ ብዙ ነገር*
*በዚያም በዚህ ቢሉት መሆኑ የማይቀር " ::*

ሁሉ ነገር ቀደም ሲል የተወሰነ ነውና የሰው ልጅ ጥረትና እንቅስቃሴ ምንም አንደምታ አይ ኖረውም ማለት ባይቻልም የሚሆን ነገር መሆኑ ደግሞ ሀቅ ነው:: በገዋ፣ በባዶ ምኞትን መጋ ለብና ሊሆን የማይችለውን ይሆናል ብሎ መገመት--መጠበቅ ከባድ ስህተት ነው:: መሆኑ የ ማይቀርንም ክስተት ደግሞ ራስን አሞኝቶ አይሆንም ማለት ሌላ ከባድ ስህተት ነው:: ወያኔ

ወያኔ መሆኑ እየታወቀ፣ ሀገርን ሊያጠፉ የመጣ ቡድን መሆኑ ግልፅ ሆኖ እያለ፣ ሀገርን ለባ ዕዳን የሚሸጥ ከሀዲ ቡድን መሆኑ በገቢር ተረጋግጦ የቀረበ ሆኖ፣ ፀረ ሕዝብ አፋኝ ዘረኛ ቡ ድን መሆኑ ለዓመታት የታየ ሆኖ ሳለ ወያኔ ሌላ ይሆናል፣ ይሻሻላል፣ ቁንጮው ሞቷልና ይ ቀየራል ብሎ ማሰቡና ማለሙ ዜጋን የሚያዘናጋ ነው:: ወያኔ ተለመነ ወይም እግዚኦ ተባለ ከወያኔነቱ ከቶም አይቀይር ። ያሳደገ ሰይጣን ሳይገድል አይተውም እንደተባለው ነው:: መ ለስን ተካ የተባለው ግለሰብ ስልጣን አልባ አሻንጉሊት ነው:: ለእሱ ጊዜ እንስጠው ያሉና የቋ መጡ ሆዳሞች ራሳቸውን አጋልጠዋል፣ ቀለዋል:: ስልጣን ዛሬም ቢሆን በዘረኛው ወያኔ እጅ ነው -- በረከትና ስብሐት ቢራኮቱም መሰረታቸው ወያኔነት ነው:: ወያኔ ከስልጣን እስካልተ ወገደ ድረስ ወያኔነቱ የማይለወጥና የማይቀር ነው::

*" ምኞት ያረገዘው አይቀርም በከንቱ*
*የሚወለድበት ይደርሳል ሰዓቱ " ።*

ባለነፍጦች ለስልጣን በቅተው በደም እየታጠቡ ሲያጓሩ ነገር ዓለሙ አበቃ ብሎ መንበርከክ መብትና ሀገርን የሚያሳጣ ይሆናል:: ኢትዮጵያ ሀገራችን ለባዕዳን አልገዛ በማለቷ አያሌ ጠ ላቶችን እስከዛሬ አፍርታለች:: በነፃነቷ፣ በምሳሌነቷና በአፍሪካ ባላት ሚናና ሚዛን የሚጠሏ ት ብዙ ናቸው:: ምዕራባውያን በአፍሪካ ትልቆች ሀገሮች የሚባሉትን መበታተን የሚፈልጉ ናቸውና ኢትዮጵያ በዕይታቸው የገባች ናት:: መበታተኗን ይፈልጋሉ:: መዳከሟን ይፈልጋ ሉ:: የኤርትራን መገንጠል እንደደገፉ ሁሉ ሌሎችም በግንጠላ ጎዳና ቢሄዱ ቅር የሚላቸው አይደለም:: የአፍሪካ ትልቅ ሀገሮችን ማስጎንበስ፣ መገነጣጠል ይጠቅመናል ብለው ደምድ መዋል:: ሱዳንን ገነጣጥለዋል:: ናይጄሪያንና ኮንጎንም ለመገነጣጠል እየጣሩ ናቸው:: የኢት ዮጵያን ገንጣይ ሀይሎች የሚረዱት ምዕራባውያን ናቸው:: በዚህ በኩል ወያኔን ይታደጋሉ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የነሱ ሎሌ የሚሆኑትን ተቃዋሚ ነን ባዮችን ይረዳሉ:: ይህን ማወቅ ያስ ፈልጋል:: ኢትዮጵያ ሀገሬ ብሎ ፀንቶ የሚቆም ሀይል ወዳጃቸው አይደለም:: ኢሕአፓ አክራ ሪ ብሔርተኛ ተብሎ የሚወገዘው ለባዕድ ተንበርክኮ ሀገርን አሳልፎ ስላልሰጠ ነው:: ያም ሆነ ይህ ግን የወያኔ ሽንፈት ዛሬ ባይሆን ነገ እውን የሚሆን ነው:: የጊዜ ጉዳይ ነው:: የሕዝብን ቆራጥ መነሳሳትና አመፅ የሚጠብቅ ነው:: የሕዝብ ምኞት የወያኔን ውድቀት ማየት ነውና ዛ ሬ ባይሆን ነገ ወያኔ ይወድቃል:: ይህን ማመን ያስፈልጋል:: በሕዝብ አቸናፊነትና ድል አድ ራጊነት ላይ ምንም ጥርጣሬ ሊኖርም አይገባም ።

*"ሐሳቡን ሰመመን ወስዶ እየመለሰው*
*ቆይቶ ይነቃል የተታለለ ሰው"*

*ያርገው!*

*"ህብታምን በህብቱ ሁሉ ሰው ሲያደንቀው*

*ከየት እንዳመጣ ማንም አይጠይቀው"*

**ሀቅ!!**

*" ጎደሎ ከሆነ የሰው ልጅ እውቀቱ*

*ድካሙ ብላሽ ነው ስራው ሁሉ ከንቱ " ::*

ተጨማሪ የሚያሻው አይደለም :: ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ መገንዘብ መቻል አለብን:: ያለፈው ታሪክ ዋጋውና ሚዛኑ እንዳለ ሆኖ

*" ወደፊት ነው እንጂ ሌቱ የሚነጋ*

*ያለፈው ከንቱ ነው ምንም የለው ዋጋ"*

ማለትም ምናልባት አስፈላጊ ይሆናል:: የወያኔ አገዛዝ በሕዝብ ትግል የሚገረሰስ መሆኑን ማመን ወሳኝ ነው:: ይህ አምነት ትግልን ያቀጣጥላል፤ ወደ ድልም ያመራል:: ጉዞው ከባድ ነው ግን መጨረሻው የሕዝብ ድል ነው::